# ሕዝባዊ አንድነት በዘረኛና ጐጠኞች ሤራአይፈታም!

## ከኢትዮጵያ ሲቪክ ማኀበራት የጋራ መድረክ የተሰጠ መግለጫ

በታሪክ አጋጣሚ መንበረ ሥልጣን የጨበጡ አምባገነኖች እንዳሻቸውና እንደፈቀዳቸው ሕዝብን መግዛት ከማይችሉበት ደረጃ ሲደርሱ፣ በሰላምና በሕጋዊነት ሽፋን የሚገለገሉባቸው አያሌ ሴራዎችን ሲጐነጕኑ ይስተዋላል:: ጊዜው ባለፈበትና የከፋፍለህ ግዛ ስልት ጭምር ሕዝብን ከሕዝብ በማጋጨትና የአንድነትና የለውጥ አመለካከቱን በማዛባት የሥልጣን ዕድሜአቸውን ለማራዘም መውተርተራቸውም እውነት ነው:: ሕዝባዊ ተቃውሞን ለማርከስና የሥልጣን ባለቤትነቱን ለመንጠቅ ከሚካሄዱ የአምባገነኖች ደባ መካከል ዘርን፤ ብሔረሰብን ፣ ቋንቋና ሃይማኖትን በመሣሪያነት ተጠቅሞ ልዩነቶችን መፍጠርና ግጭቶችንም ማባባስ በዋነኛነት ይፈረጃሉ::ይህ ውጉዝ ያረጀና ያፈጀ የሥልጣን ጥመኞች ስልት በአንዳንድ የዓለማችን ክፍሎች በእጅጉ አሳዛኝና አሳፋሪ ውድመቶችን ከማስከተል አልፎ በሕዝቦች መካከልም የማይሽር ጠባሳ ጥሎ አልፎአል:: በዩጐዝላቪያ፣ በቦስኒያ ሔርዞጐቪና በሩዋንዳ በሶማሊያና በሱዳን ሕዝቦች ዘንድ ከታዩት የእርስ በርስ ግጭቶችና መጠነ ሰፊ ጥፋቶች መላው ዓለምና እንደዓለምአቀፍ ሕብረተሰብ አባልነታችን እኛ ኢትዮጵያውያንም በዙ ልንማር ብሎም ከመሰል የጥፋት ማጥ ውስጥ እንዳንዘፈቅ ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ ከሚገባን ወቅት ላይ እንገኛለን::

በአገራችን ሰላማዊና ዲሞክራሲያዊ የሥልጣን ሽግግር ዕውን ይሆን ዘንድ ተስፋ የተጣለበት አገር አቀፍ ምርጫ፣ ከድምፅ አሰጣጥ በኋላ በተከሰቱ የድምፅ ቆጠራና ውጤት ላይ በተመረኰዙ ውስብስብ ችግሮች ተተብትቦ ይገኛል:: የችግሩ ብቸኛ ቁልፍና አማራጭ የሌለው ዋነኛ መፍትሔ ደግሞ አንድ ብቻ ነው:: የሕዝብ ድምፅ መከበር!! ሕዝብ በድምፁ የሰጠው ይግባኝ የሌለው የማይገለበጥና ለድርድር የማይቀርበው ብይን መከበርና ተግባራዊ መሆንም አለበት::

የሕዝብ ድምፅ ከዲሞክራሲያዊና ከነፃ ዜጋ መብትነት ባሻገር፣ የፍላጐቱ መገለጫና የሥልጣን ባለቤትነቱ ማረጋገጫ ነው:: ይህን ታላቅ የሕዝብ መብትና የሥልጣን ባለቤትነት በመግፈፍ አምባገነናዊነትን ለማስፈን ያመች ዘንድ ተከባብሮና ተፈቃቅሮ በሚኖር ሕዝብ መካከል የጥላቻ ዘር ለመዝራት የሚካሄድ የየትኛውም ወገን አደገኛ ተግባር ሁሉ ያለርህራሄ መምከን ይኖርበታል:: ለኢትዮጵያ ሕዝብ ዕድገትና ብልጽግና ቆመናል የሚሉ ግለሰቦች፣ የፖለቲካ ድርጅቶችም ሆኑ የሲቪል ተቋማት ሁሉ እንዲህ ዓይነቱን ለሥልጣን የቋመጡ ሴሬኞችና የጥፋት መልዕክተኞችን ውጥን አምርረው መታገል ይጠበቅባቸዋል:: ሕዝብን ዘረኝነት ወደ ተጠናወተው ግጭት መገፋፋትም ሆነ የኢትዮጵያ ሕዝብን የለውጥ ፍላጐትና እንቅስቃሴ በአንድ አካባቢ ሕዝብ ላይ እንደተወጠነ ሰይጣናዊ ድርጊት አስመስሎ የልዩነት ነጋሪት መጐሰም አገር አፍራሽ ሴራ ነውና ሕዝብ በግንባር ሊፋለመው ግድ ይሆናል::

በሕዝብ መካከል ፀረ- አንድነትና ዘረኝነት የተጠናወተው ቅስቀሳ ማካሄድም ሆነ ልዩነትን ማራገብ፣ ሰንካላና ሕዝብ አንቅሮ የተፋው፤ በአኳያው ግን የሥልጣን ጥመኞች ደም ሥርና ልፍስፍስ ፖለቲካቸው አስኳል ነው:: ሕዝባዊ ሥልጣን ለመጨበጥም ሆነ የሕዝብን አመኔታና ክብር ለመቀዳጀት ብሎም ሃገርን በዕድገትና ብልጽግና ጐዳና ለማራመድ ወሳኙ መስፈርትና ሚዛን አንድ ነው:: ይህም በሃገርና ሕዝብ ፍቅር የነደደ ኢትዮጵያዊ ልብና ዲሞክራሲያዊ አስተሳሰብ የተጋራ ራዕይ ነው:: ከዚህ ባለፈ ተባብሮ ተፋቅሮና ተሳስቦ በመኖር የወደር የለሽ ታሪክ ባለቤት በሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ መካከል አሳፋሪውን የጥላቻ ዘር በመዝራት አንድነቱን ለማናጋት የሚቅበዘበዙ ኃይሎች ሁሉ ከእኩይ ተግባራቸው ሊቆጠቡና የጥፋት አንደበትና እጃቸውንም ፈጥነው ሊሰበስቡ ይገባል::

የኢትዮጵያ ሲቪክ ማኀበራት የጋራ መድረክ የወቅቱ አምባገነን ገዥዎች፤
የሥልጣን ጥመኞችና ፀረ - ኢትዮጵያ ስብስቦች የሚያውጠነጥኑትን ሕዝብን የመከፋፈልና ወደማያባራ የእርስ በርስ ውዝግብ የሚያመሩ ፀረ- ዲሞክራቲክ ድርጊቶችን አጥብቆ በማውገዝ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ ለመብቱ ለነፃነቱና ለብሔራዊ ክብሩ የሚያካሂደውን ሁለገብና ዲሞራሲያዊ እንቅስቃሴ በፅናት አጠናክሮ እንዲቀጥል ጥሪውን ያቀርባል::

የኢትዮጵያ ሕዝብ ድምፅ ይከበር!
የኢትዮጵያ ሲቪክ ማኀበራት የጋራ መድረክ

(አንጋፋው የኢትዮጵያ መምህራን ማኀበር/ኢመማ/፤የኢትዮጵያ ነፃ ፕሬስ ጋዜጠኞች ማኀበር/ኢነጋማ/፤የኢትዮጵያ ሃገራዊ ጉባኤ/ኢሃጉ/፤ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ወጣቶች ማኀበር፤የኢትዮ አሜሪካውያን ሕብረት፤ኢትዮጵያን ሪቪው)

ሰኔ 21 ቀን 1997 ዓ/ም -አዲስ አበባ